የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
DEVELOPMENT BANK OF ETHIOPIA

# የጥያቄዎቻችሁ
# መልሶች

በሦስተኛው የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠና ላይ ከሠልጣኞች ተነሥተው ለነበሩ ጥያቄዎች በባንኩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው የተሰጡ መልሶች

ግንቦት 5 ቀን 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መግቢያ

ልማትን በሚፈለገው ደረጃ ለማረጋገጥ ዕውቀትና ክህሎት መሠረት መሆናቸውን የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እንደ መርኅ ይዞ እየሠራባት ይገኛል። ለዚህም ማሳያው ደግሞ የባንኩ አገልግሎት መለያ እስከሚሆን ድረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ ቦታ የተሰጠው የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠና ነው።

ሥልጠናው ካለው ፋይዳ አንጻር በሁሉም ክልሎች ተደራሽ እንዲሆንና በሠልጣኞችና በሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትኩረት እንዲሰጠው ሆኗል። ሥልጠናው በሀገር ደረጃ ልምድና አቅሙ ያላቸው ድርጅቶች በሚያሰማሯቸው ምሁራንና ባለሙያዎች ይሰጣል። በሥልጠናው በተለያየ የሥራ መስኮች ላይ የተሰማሩ፣ የመሰማራት ፍላጎት ያላቸው፣ በዕድሜና የትምህርት ደረጃ የተለያየ ስብጥር ያላቸው ሠልጣኞች የሚታደሙ ሲሆን፣ እነዚህን አቀራርቦና፣ አጣጥሞ በሥልጠናው የሚገኘውን ዕውቀት ለመስጠት ጥረት ይደረጋል። እስከ አሁን በሦስት ዙር ሥልጠናዎች የተካሄዱ ሲሆን 33 ሺህ ያህል ሠልጣኞች ሠልጥነዋል።

በሥልጠና መድረኮቹ ከሚቀርበው ዕውቀት ባሻገር ስለባንኩ አገልግሎት በጥልቀት ለማወቅ በሠልጣኞች በኩል ያለ ፍላጎት የሥልጠና መድረኩን ሞገስ ያላብሰዋል። ሠልጣኞች ባንኩ ስለሚሰጠው አገልግሎት፣ ከእነርሱ ጋር ለመሥራት ስላለው ዝግጁነት፣ ስለሚከተላቸው ፖሊሲዎች፣ ስለነባርና አዳዲስ የተዘረጉ አሠራሮች ለማወቅ የባንኩን ፕሬዝዳንት በቀጥታ ጠይቆ ለመረዳት በሦስቱም ዙሮች በጥብቅ የሚፈልጉት ነገር ነበር። ጥያቄዎች ከሁሉም ማእከላት በዙም ይቀርባሉ፤ ክቡር ፕሬዝዳንቱ በቀጥታ ይመልሳሉ። በዚህ ምክንያት ግልጽነት ለመፍጠር አመቺ መድረክ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ሚዲያና ኮምዩኒኬሽንስ ዳይሬክቶሬት እነዚህ ጥያቄዎች በቀደሙት ዙሮች ለነበሩ ሠልጣኞች ብቻ ሳይሆን በቀጣይ ዙር ለሚመጡ ሠልጣኞችም ቀድሞ መረጃ ለመስጠት እንደሚጠቅሙ ያምናል። አዳዲስ ሠልጣኞች ቀድሞ ማብራሪያ ከተሰጠባቸው ጥያቄዎችም መረጃዎችን በማግኘት ሌሎች ሽፋን ላልተሰጣቸው፣ ወሳኝ ለሆኑና የበለጠ መብራራት አለባቸው በሚሏቸው ጥያቄዎች ላይ በማተኮር መድረኩን በበቂ እንዲጠቀሙበት ለማስቻልም ይጠቅማል። በመሆኑም ጥያቄና መልሶችን በአንድ ቡክሌት አዘጋጅቶ ማሳተም ስለሚጠቅም ይህ ኅትመት ተዘጋጅቷል።

አንባብያን በሥልጠና መድረኮቻቸው ብቻም ሳይሆን ሌሎች ከሥልጠናው መድረክ ውጪ የሚገኙ፣ በኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሽነት ለመሳተፍ ዝንባሌና ፍላጎት ላላቸው ሁሉ እንደ መረጃ መስጫ እንደሚያገለግልም ይታመናል።

መልካም ንበብ !



**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው**

**ፕሬዝዳንት**

■ **ጥያቄ፦** አብዛኞቹ ሠልጣኞች ሥራ የሌለንና መነሻ ካፒታል የምንቸገር ነን፤ ሥልጠናውን የምንወስደው ወደ ሥራ መግባት ፈልገን ነው። ታዲያ የ20 በመቶ መዋጮን ስለምንቸገር ባንኩ እንዴት ሊደግፈን ይችላል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ እኛም በሥራው ሂደት ያስተዋልነው ወደ ሥራ መግባት እየፈለጋችሁ የፋይናንስ አቅም ችግር እንዳጋጠማችሁ ነው፤ ለዚህ ግን ባንኩ በየክፍሉ የሚሄድበት፣ በሽርክና (በኅብረት ሥራ) አቅም ፈጠራችሁ ወደ ሥራው የምትገቡበትን አሠራር አዘጋጅቷል። 10 ወይም 20 ወይም 30 ሆናችሁ በሽርክና ድርጅት ማቋቋም ትችላላችሁ፤ ከዚያም ባንኩ ያግዛችኋል። 20 በመቶ የሚባለውን ነገር በቀላሉ ማግኘት ትችላችሁ ማለት ነው።

ሽርክና ግን ዘመናዊ በሆነ አመራር መመራት አለበት። የራሱ ቦርድና ማኔጅመንት ቡድን ይኖረዋል ማለት ነው። ቦርዱ የፖሊሲ ጉዳዮችን ይወስዳል፤ ማኔጅመንቱ ደግሞ ተግባሩን ይመራል። ይህ በተለይ ከዩንቨርሲቲ ተመርቀው ለሚወጡ አዳዲስ ምሩቃን ማለትም ካፒታል ገና ላልፈጠሩ ሁሉ አንድ ዕድል ነው። ከዚያ በኋላ የራሳቸውን ካፒታል ይፈጥራሉ። በሂደት ድርጅቱን ከአነስተኛ ወደ ትልቅ ድርጅት እስከማሳደግ ይደርሳሉ። በሂደት ውስጥ ባንኩ አብሯቸው ይጓዛል። ወደ ትልቅ ደረጃ ሲሻገሩም የሚያሻግራቸው ባንኩ ይሆናል።

ዓላማችን ሀገራችን ያለባትን የካፒታል እጥት መቅረፍ ነው፤ ካፒታል የሚፈጠረው ኢንቨስት በማድረግ ነው። እናንተ 20 በመቶ ብታዋጡም 80 በመቶውን ባንኩ የሚሰጣችሁ በመሆኑ የባንኩ ሥራ አብሯችሁ ኢንቨስት በማድረግ ለሀገራችን ካፒታል መፍጠር ነው። ባንኩ የሰጣችሁን 80 በመቶ በኪራይ ስትጨርሱ ያ፤ ባንኩ ሰጥቷችሁ የነበረውና አሁን ከፍላችሁ ስትጨርሱ ሀብት ያደረጋችሁ 80 በመቶ ለእናንተ ካፒታላችሁ ይሆናል። ስለዚህ ከሃያ በመቶ ወደ መቶ በመቶ የካፒታል አቅም ደረሳችሁ ማለት ነው። በዚህ በመቶው ባገኛችሁት ካፒታል ደግሞ የተሻለ ሌላ ብድር ታገኙበታላችሁ።

የቀደመው 20 በመቶ መዋጮ ሁለት ሚሊዮን ቢሆን፣ ባንኩ የሚሰጠውን የስምንት ሚሊዮን ብር ኪራይ በመመለስ ማሽነሪውን የራሳችሁ ስታደርጉ በቀጣይ የ10 ሚሊዮን ካፒታል ባለቤት ሆናችሁ ማለት ነው።

እናንተ ያገኛችሁት 10 ሚሊዮን ካፒታል ደግሞ የሀገርም ነው። በሥራችሁ በሀገር ካፒታል ላይ 10 ሚሊዮን ተጨማሪ ፈጠራችሁ ማለት ነው። ሌሎች ሀገራት የተጓዙት በዚሁ መንገድ ነው። ችግሩ ግን ተበዳሪ የተሰጠውን ብድር የማይከፍል ሲሆን ነው። ብድር ክፈሉ ስንል አትጎዱ፣ ሀገርም አትጉዱ፣ የተሻለ ካፒታል ፈጥራችሁ ዕደጉ ማለታችን ነው።። ብድር የማይመልስ ካፒታል የመፍጠር አቅም አጥቷል ማለት ነው።

የማደግ ምስጢሩ ይኸው ነው። እናንተ ትርፍ ስታገኙ ደግሞ ታክስ ትከፍላላችሁ፤ ታክስ ከከፈላችሁ ደግሞ መንግሥት በቀላሉ መንገድ ይሠራል፤ ትምህርት ያስፋፋል፤ ሌላም የልማት ሥራ ይሠራል። እናንተ ድርጅታችሁን ከፈታችሁ፣ አሳደጋችሁ፣ አስፋፋችሁ ማለት ብዙ ሠራተኛ ትቀጥራላችሁ። በዚህ የሥራ ዕድል ጨመረ ማለት ነው። ሠራተኛ በዛ ማለት ምርት የመግዛት ፍላጎት ጨመረ ማለት ነው፤ የራሳችሁን ምርት ይገዛችኋልና። እናንተ ካፒታላችሁን ጨምራችሁ አስፋፍታችሁ ስትሠሩ ምርት ይጨምራል፤ ምርት ጨመረ ማለት ደግሞ የገበያ ዋጋ ይረጋጋል። የእናንተም የሕዝቡም ኑሮ የተሻለ ይሆናል። የእናንተ ምርት የሚያድግ ከሆነ ግብዓት የምታገኙበት ሴክተርም ያድጋል። ለምሳሌ ዘይት ማምረቻ ከሆነ የከፈታችሁት ግብዓቱን ከግብርና ታገኛላችሁ። ስለዚህ የእናንተ ማደግ ግብርናውም እንዲያድግ ይረዳዋል። ለኢንዱስትሪም እንደዚያው ነው። ጥሬ ዕቃ አቅራቢው ልትሆኑ ትችላላችሁ። ዋናው አውቆ አቅዶ መምራት ያስፈልጋል። ሥራን በዕውቀት መምራት ያስፈልጋል።

እውቀት ከትምህርትና ሥልጠና ይገኛል። አሁን በምትሠለጥኑበት መንገድ ለሥልጣና ጊዜያችሁን ስጡ። የትም ቦታ ላይ ለአንድ ሰዓትም ቢሆን ትንሽ ነገር ታገኛላችሁ፤ መሠልጠንን፣ ሠራተኞቻችሁን ማሠልጠን ሥራችሁ አድርጋችሁ መያዝ ያስፈልጋችኋል።

- ጥያቄ፦ ባንኩ ለአካል ጉዳተኞች ምን የተለየ ፕሮግራም አለው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንኩ ለምሳሌ ባለሙያዎች ሲቀጥር ለአካል ጉዳተኞች ለሴቶች የተለየ ትኩረት ይሰጣል፤ ያበረታታል። ተጨማሪ ነጥብ ሰጥተን እናበረታታለን" ከሥራ አንጻር ስናየው አካል ጉዳተኞች ተወዳዳሪ አይሆኑም አይባልም። አካል ጉዳተኞች ለእነሱ የሚመች የቢዝነስ ዓይነት መምረጥ አለባቸው። አዋጪ ቢዝነስ መምረጥ አለባቸው። ተወዳዳሪ እንደሚሆኑ እናምናለን። ለጊዜው ግን በተለየ መንገድ የምናይበት አሠራር የለም። ምክንያቱም አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ሲባል በዝቅተኛ ወለድ የምንሰጥበት አሠራር ነው።

በሀገር ደረጃ አሁን ብድር የሚሰጠው ከ18 በመቶ በላይ በሆነ ወለድ ነው። እኛ ግን የምናሰላው ከፍተኛው 11 ነጥብ 5 በመቶ ነው፤ እስከ 9 በመቶም የሚወርድ አለ። እኛ የምንሠራው ለትርፍ አይደለም፤ ለማምረት ነው። ከዚህ በታች መውረድ አንችልም። ከዚህ በተጨማሪ ማስያዣ (ዋስትና) አንጠይቃችሁም። ማስያዣው ማሽኑ ነው፤ ወይም ፕሮጀክቱ ነው። ስለዚህ ከእናንተ የሚጠበቀው የሥራ ማስኬጃ ነው። የሥራ ማስኬጃው የእናንተ እንዲሆን የተፈለገበት ምክንያት ደግሞ ለሥራው ዝግጁ መሆናችሁን የምንለይበት መንገድ የመሥሪያ ካፒታል በመያዛችሁም ነው። ካልሆነ ግን ለማንኛውም ሰው መስጠት አለበት ማለት ነው።

የምንጠይቃችሁ መዋጮ ደግሞ የሚያገለግለው ለባንኩ አይደለም፤ ለራሳችሁ ነው። ለሠራተኛ፣ ለቤት ኪራይ፣ ለጥሬ ዕቃ ወዘተ የምትከፍሉት ነው። መንግሥት ደግሞ መንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ ሼድ ያግዛችኋል። ይህ አጠቃላይ ስናየው እገዛ ነው፤ ስለዚህ አካል ጉዳተኞችም የዚህ እገዛ ተጠቃሚዎች ናቸው። ስለዚህ ይህ በተለየ ሁኔታ እናንተም ካፒታል እንድትፈጥሩ ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር የፈጠረላችሁ ፕሮግራም ነው። ወደፊት ለአካል ጉዳተኞች ብለን የምናየው የተለየ ነገር የሚኖር ከሆነም በጥናት እናየዋለን።

- ጥያቄ፦ በሊዝ ፋይናንስ አሠራር ጥሬ ዕቃ የሚገዛበት ብድር አለ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንኩ ማሽነሪ ከሰጠ፣ ማስያዣ ካልጠየቀ፣ ጥሬ ዕቃም ከሰጠ የብድር ጠያቂው ጥረት የሚታየው ምን ላይ ነው? 20 በመቶው መዋጮ እኮ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፤ ለጥሬ ዕቃውም ነው። 20 በመቶው አዋጥታችሁ ወደ ሥራ ገብታሁ ከሁለት ዓመታት በኋላ ውጤታማ ከሆናችሁና የማደግና የመስፋት እምቅ አቅም መፍጠራችሁን ሲያረጋግጥ ግን ባንኩ ብድር አመቻችቷል። ሁለት ዓመታት ከሠራችሁ፣ ብድራችሁን እየመለሳችሁ መሆኑ ስለሚታይ ባንኩ ያላችሁን አቅም አይቶ ለጥሬ ዕቃ ተጨማሪ ብድር አመቻችቷል። መጀመሪያ መፈተኛችሁ ግን 20 በመቶው ነው።

- ጥያቄ፡- የራሳቸው የመሥሪያ ቦታ የሌላቸው ኢንተርፕራይዞች በምን መልኩ የካፒታል እቃ ኪራይ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፡- የራሳቸው መሥሪያ ቦታ የሌላቸው ኢንተርፕራይዞች በኪራይ ቦታ ላይ መሥራት እንዲችሉ ባንኩ የአሠራር ማሻሻያ አድርጓል። በመሆኑም የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ለማዋጣት አቅም ያላቸው ኢንተርፕራይዞች ምንም እንኳ የራሳቸው የሆነ የመሥሪያ ቦታ ባይኖራቸውም የኪራይ ውል በማቅረብ ከባንኩ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ።

- ጥያቄ፦ ከማምረቻ ቦታ ጋር ተያይዞ ቢያንስ ለ6 ዓመታት የኪራይ ውል እንጠየቃለን፤ ለኪራይ ስንሄድ ደግሞ እየተቸገርን ነው፤ ይህ የሚሻሻልበት ሁኔታ ይኖራል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ በኪራይ ማሽነሪ እንሰጣችኋለን። ማሽነሪው ግዙፍ ሲሆን እንዳይነቃነቅ ሆኖ ይተከላል። የረጅም ጊዜ ውል ከሌላችሁ ማሽነሪ ማንሣት ቀላል አይደለም፤ ሲነሣ ይበላሻል። አምስት ዓመት ስድስት ዓመት ስንላችሁ የቆየነው ማሽሪ ማንሣት ጉዳት ስላለው ነው። አሁን ግን የእናንተን ችግር አይተን አሻሽለነዋል፤ ወደ ሁለት ዓመታት እንዲወርድ አድርገነዋል። ይሄ ሁለት ዓመት የመዘጋጃ ጊዜ እንዲሆነን ነው። ከክልሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነት ብዙ ሼዶች እንዲሠሩ፣ እኛም ማገዝ ካለብን እያገዘን ችግሩን ለመፍታት እንጥራለን። ሼዶቹ ካሉ እናንተ እንድትይዙ ለማድረግ ነው። መፍትሔ ለመስጠት የሞከርነው የቤት ኪራይ ጉዳይ አሳሳቢ መሆኑን እኛም ስላወቅን ነው።

- ጥያቄ፦ የገቢ ምርትን ከመተካት አንጻር በተለይ በሀገር ውስጥ ማሽነሪ የሚመረትበትን አሠራር የባንኩ ፖሊሲ እንዴት ያየዋል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ እኛ ማሽነሪዎች ሀገር ውስጥ እንዲመረቱ እናበረታታለን። እኛ በሀገር ውስጥ ማሽነሪ ከሚያመርት በርካሽ ገዝተን፣ የውጪ ምንዛሬ ፍላጎታችንንም ቀንሶልን እንዲሠራ ነው የምናበረታታው። በዚህ መንገድ የጀመሩ አሉ፤ ግን የምንፈልገው ደረጃ ላይ አልደረስንም። ማሽሪዎችን ከሀገር ውስጥ መግዛትን እያበረታታን ተወዳዳሪ ካልሆነ ግን አንገዛም። ማሽነሪውን እኮ ገዝተን የምንሰጠው ለእናንተ ነው። ማሽነሪው ጥራትና ዕድሜ ከሌለው መልሶ የሚጎዳው እናንተንም ነው። ጥራት ከሌለው ልትፈጥሩ የፈለጋችሁትን ካፒታል መፍጠር አትችሉም። ስለዚህ የሀገር ውስጥ አምራቾች በዓለም አቀፍ መስፈርት ተወዳድረው ካሸነፉ ደስ ብሎን እንገዛቸዋለን።

- ጥያቄ፦ የራሳችን መሥሪያ ቦታ ቢኖረን እና ከሌላ ባንክ ብንበደርበት ምን ችግር አለው፤ በኪራይ ለሚሠሩት ተፈቅዶላቸው ሳለ ለምን ይህ ይከለከላል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ በእኛ ማሽን እየሠራበት ባለው ቦታ




# Supporting Agriculture Through 'Lease Finance'

ሌላ ባንክ ተበድሮበት ከሆነ ችግር ሲያጋጥም አበዳሪው ባንክ ቦታውን ልውሰደው ቢል የሚሆነው ማሽናችንን አስወጥቶ ሥራ አስቁሞ ነው፤ ይህ ችግር ይሆንብናል በሚል ነው። ልማት ባንክ ምንም ማድረግ አይችልም። በሕግም ለዋስትና የተሰጠ ከሆነ መከልከል አይቻልም። እናንተ ያነሳችሁትን ጥያቄ ግን እኛ አስበንበት ቆይተናል፤ በመሆኑም የተወሰነ ማሻሻያ ተደርጓል። በዋስትና የተያዘ ቢሆንም ብድሩን በጥሩ ሁኔታ እየከፈለ መሆኑን ማረጋገጫ የሚሰጠን ከሆነ፣ በባንካችን ክትትል ይህ የተረጋገጠ ከሆነ፣ በብድር የተያዘ ቢሆንም የሼድ ዝግጅት ጉዳይ እስከሚፈታ ድረስ ተፈቅዷል። ይህ ለጊዜው መፍትሔ ለመስጠት ነው። ያ፤ ሲሆን የቆየበት ምክንያት ግን አስቀድሜ በገለጽኩት መንገድ ልትረዱት ይገባል። የብድር አከፋፈሉን ግን ባንኩ ይከታተላል፤ ማሽነሪው አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ይፈልጋል።

■ **ጥያቄ፦** የቤት ልማት ችግርን ከመፍታት አንጻር ባንኩ ለምን አይሳተፍም?

**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦** እኔም ይህንን መሠረታዊ ችግር ከመፍታት አንጻር ቢሠራ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ሀብት ውስን ስለሆነ ሁሉም ልማት ውስጥ መሳተፍ አይቻልም። የቤት ልማት የሚጠይቀው ገንዘብ ቀላል እንዳይመስላችሁ። ሐሳቡ ሳይነሣ ቀርቶ አይደለም፤ ግን ወደፊት ገንዘብ የሚገኝበት የተለየ ፕሮግራም ካለ፣ እኛም የምናግዝበት ሁኔታ ካለ ወደፊት የሚታይ ይሆናል። አሁን ግን በቅርብ ጊዜ እንገባለን ብለን አናስብም። ሌሎች በቤት ልማት ላይ ያሉ ፕሮግራሞች እየተስፋፉም ስለሆነ በእነሱ ይሸፈናል ብለን እናስባለን። ነገሩ አቅም ይፈልጋል። አሁን ባለን አቅም ደግሞ በግብርና ኢንዱስትሪው ላይ ያለውን ችግር መቅረፍ ላይ እናንተኩራለን።

■ **ጥያቄ፦** በጦርነት በተጎዱ አካባቢዎች ላሉና ጀማሪ ሥራ ፈጣሪ ለሆኑ ሠልጣኞች ምን የተለየ ድጋፍ ይደረግላቸዋል?

**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦** በጦርነት አካባቢዎች ብዙ ጉዳቶች መድረሳቸውን እናውቃለን፤ ለዚህም እውቅና እንሰጣለን። ነገር ግን ባንኩ የሚሠራው ባንክ ስለሆነ የባንክ ባህሪውን ጠብቆ ነው። በጦርነት አካባቢዎች በደረሱ ጉዳቶች ሰዎች

ተዘርፈዋል፤ ሀብታቸው የወደመባቸው አሉ፤ ይሄ ይታወቃል። ነገር ግን የባንክ አሠራር እንዳለ ሆኖ የ20 በመቶ መዋጮው እንዴት መሆን እንዳለበት ከሚመለከታቸው ጋር እንመክራለን። ባንኩ ብቻውን የሚያደርገውና ሁሉን የሚሸፍንበት ሁኔታ አይኖርም። ነገሩን በዚህ ደረጃ መረዳት፣ በዚህም መዘጋጀት ያስፈልጋል። 20 በመቶውንም እናሟላለን አንልም። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች ግን እንዴት 20 በመቶውን ያሟሉ በሚለው ላይ ከሚመለከታው ጋር የምንወያይት ይሆናል። ሐሳባችሁን ባንኩ ላይ ብቻ አትጣሉ፤ በእናንተም በኩል ከሚመለከታቸው ጋር ለመወያየትም ሞክሩ።

■ **ጥያቄ፦** ዝቅተኛው መሥሪያ ካፒታል ሁለት ሚሊዮን ነው፤ ሁለት ሚሊዮን ከሆነ ሁለት ሚሊዮን ብር ለማዋጣት ያስቸግራል፤ እንዴት ይሆናል?

**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦** እኛ ያስቀመጥነው መነሻ ካፒታል 500 ሺህ ነው። 500 ሺሕ ይዞ የመጣ ሁለት ሚሊዮን ያገኛል አልን እንጂ፤ የግድ ሁለት ሚሊዮን ይዞ ይምጣ አላልንም። ስለዚህ 500 ሺህ ያለው ሰው ሲበደር በአጠቃላይ 2.5 ሚሊዮን ይኖረዋል ማለት ነው። ሁለት ሚሊዮኑ ማሽን መግዣ ነው። ስለዚህ ዐሥር ሰዎች ቢሰባሰቡ እያንዳንዳቸው 50 ሺሕ ብር ቢያዋጡ 500 ሺሕ ብር ማዋጣት ይችላሉ። ሁሉም ደግሞ ሃምሳ ሺህ ብር ባይችሉ የተወሰኑት መቶ ሺህ ሊያዋጡ ይችላሉ። ዝቅተኛ ያዋጡት ሼራቸው ይቀንሳል እንጂ የዚያ ሥራ አካል ይሆናሉ ማለት ነው።

አክሲዮን ሲባል የግድ የሁሉም መዋጮ እኩል መሆን አይጠበቅበትም። ዐሥር ሺህም ይዞ ሊገባ ይችላል። ምንአልባትም ተቀጥሮ ደግሞ በሥራው ውስጥ ደሞዝ ሊያገኝ ይችላል። በደሞዝ ከሚያገኘው ደግሞ ሼሩን፣ ካፒታሉን እያሳደገ ሊሄድ ይችላል። ይህንን እናግዛችኋለን። ከኢንፎርሜሽኑ ጀምሮ አመራርን ጨምረን ማገዝ እንችላለን። መቼም ከአንድ ዩንቨርሲቲ የወጣ ሰው እንደተመረቀ የሆነ ነገር ማድረግ አለበት። ቢያንስ በዚያ ድርጅት መቀጠር አለበት። ሥራውን በዕውቀት እንምራው ስንል ምሩቃን በእንደዚህ ዓይነት ሥራዎች ውስጥ እንደምንም መግባት አለባቸው ማለታችን ነው። በሒሳብ አያያዝ የተማረ ሰው በአክሲዮን ሼሩ ዝቅ ያለ ቢሆን በዚያ ድርጅት ተቀጥሮ የሒሳብ ሥራውን እርሱ መሥራት አለበት። በማኔጅመንት የተመረቀው የማኔጅመንት ሥራውን፣ በሰው ኃይል አስተዳዳር የተመረቀ የሰው ኃይል ጉዳዩ ላይ መሥራት ያለበት እርሱ ነው። እያደረግን ያለነው እዚህ ተቀጥሮ፣ ሼር ገዝቶ ደግሞ ባለቤት የሚሆንበት አሠራር እንዲኖር ነው።

ማወቅ ያለባችሁ ብዙ መንገድ አለ። መንገድ ብቻ ሳይሆን ገንዘቡም አለ። ስለዚህ አቋራጭ አትፈልጉ። እኛ ሀገር የገባው ችግር ይሄ ነው፤ ሠርተን እናድጋለን በሉ። በማንኛውም መንገድ ቢሆን የድርጅት ባለቤት መሆን ትችላላችሁ። ሠርታችሁ ሼራችሁን ማሳደግ ነው። እስከቻላችሁ ድረስ በአንድ ድርጅት ብቻ አይደለም በሌሎችም ድርጅቶች ሼር ሊኖራችሁ ይገባል። የሚከለክላችሁ የለም። ዋናው ግን ሀገራዊ ዓላማውን መዘንጋት የለባችሁም። ልማት ባንክ የሚሠራው ሀገራዊ ካፒታል የመፍጠር ሥራውን የማፋጠን ሥራ ነው። ለዚህ ደግሞ እናንተ መሠረት ናችሁ ብሎ ስለሚያምን ነው። አንድ ትልቅ ድርጅት ላይ በሁለት ቢሊየን በሦስት ቢሊዮን ቢቋቋም የምናገኘው ግን ሁለት ሦስት ሥራ ፈጣሪ (ኢንተርፕርነር) ነው። ይህ ግን በዝቅተኛ ካፒታል መሥራት ለሚፈልጉ እናንተን ለመሰሉ አንቀሳቃሾች ቢሰጥ እጅግ ብዙ ቢሊዮኖች የማንቀሳቀስ እምቅ አቅም ያላቸውን በርካታ ሥራ ፈጣሪዎችን ወደ ሥራ ለማስገባት ያስችለናል። ለዚህ ነው በተለይ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በተለየ የምንደግፈው፤ ለዚህም ነው ሥልጠና ለእናንተ ብቻ የምንሰጠው።

እናንተ ፕሮፖዛላችሁን አቅርቡ። ሰው ሊሞላላችሁም ይችላል፤ ላይሞላላችሁም ይችላል። ካልሞላላችሁ <በዚህ ፕሮፖዛላችን አብሮ የሚሠራ ፈልጉልን> ብትሉን በሌላ በኩል የሚፈልጉ ሰዎች ሲመጡ በእኛም በኩል እናገናኛችኋለን። በዋና መሥሪያ ቤትም፣ በዲስትሪክቶችም በቅርንጫፎችም ሥራችን ብለን የምንሠራው ይሆናል። ስለዚህ የካፒታል ገበያውንም በትንሹ እንጀምረዋለን ማለት ነው። እናንተ ቁርጠኝነቱ፣ ዕውቀቱ ይኑራችሁ።

■ **ጥያቄ፦** የሥራ ፈጠራ ሐሳብን ፋይናንስ የማድረግ አገልግሎት የሚጀመረው መቼ ነው?

**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦** ሐሳብን ፋይናንስ ማድረግ ስንል ፈጠራን ፋይናንስ ማድረግ ማለታችን ነው። ይህም የፈጠራ ባለቤት መሆን ይጠይቃል። የፈጠራ ባለቤት መሆኑን ከሳይንስና ቴክኖሎጂ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካገኘ ወይም እኛ ባለቤት መሆኑን ካረጋገጥን እርሱን ፋይናንስ የምናደርገው መቶ በመቶ ነው። የፈጠራ ሐሳቡ ማስያዣ ይሆናል። እኛ ሐሳቡን ይዘን ነው የኪሳራ ስጋቱንም የምንወስደው። ስለዚህ ሐሳቡን በፕሮጀክት መልክ ለገበያ እንዲሆን እናደርገዋለን ማለት ነው። ወደ ገበያ ሲወጣም አሸንፎ እንዲወጣ ጥረት እናደርጋለን።

■ **ጥያቄ፦** ጤና፣ ሆቴልና ትምህርት ዘርፎች በድጋፋችሁ ለምን አይካተቱም?

**ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦** አዲስ የፖሊሲ ማሻሻያ ሥራዎች እየሠራን ነው። አሁን በጤና ልንገባ ነው። ከዩንቨርሲቲዎች በሐኪምነት፣ በነርስነት ተመርቀው አሁን ሥራ ያጡ ወጣቶች እንዳሉ እናውቃለን። እነዚህን ሰዎች አደራጅተን መካከለኛ ክሊኒክ ማቋቋም፣ በላብራቶሪና መሰል ሥራዎች እንዲሠማሩ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ለማካተት ዝግጅት እያደረግን ነው። ሌላው እያሰብን ያለነው በምሕንድስና ዘርፍ ነው። በዚህ መስክ ያሉ ምሩቃን ኢንተርፕራይዝ ሆነው በሙያቸው እንዲሠሩ እየታሰበ ነው።

በሆቴል ዘርፍ ግን አንገባም። ለዚህ የሚሆን ብድር ደግሞ

ማንኛውም ባንክ ሊሰጣችሁ ይችላል። እኛ የምንሠራው መደገፍ ለሚገባው ነው። ሌላ አማራጭ(ደጋፊ) በቀላሉ በሚገኝላቸው ዘርፎች ውስጥ አንገባም። የፖሊሲ ባንክ ነን፤ የፖሊሲ ባንክ ደግሞ ገበያው የማያስተናግዳቸው ነገር ግን አስፈላጊ ዘርፎችን ለመደገፍ የተቋቋመ ማለት ነው። ገበያው የማያስተናግዳቸው ማለት ለምሳሌ ወደ ንግድ ባንኮች ስትሄዱ ማስያዣ ልትጠየቁ ትችላላችሁ 20 በመቶ ወለድ ልትጠየቁ ትችላላችሁ። በዚህ ገበያው ገፋችሁ ማለት ነው።፡ እኛ እንዲህ በገበያው የተገፉ ግን አስፈላጊ ሥራ የሚሠሩትን መደገፍ ነው።

ገበያው ሆቴልን አይገፋም። ሴክተሩ አገልግሎት ነው። አሁን ሆቴልን መደገፍ ዓላማችን አይደለም። ለጊዜው ገበያው የማይቀበላቸው እንደገፋለን። ሠርተው ካፒታል መፍጠር ሲችሉ ገበያው ይቀበላቸዋል። ዛሬ የማይቀበላችሁ ገበያ ወደፊት ውጤታማ ስትሆኑ መገፋት ሳይሆን ለምኖ ይቀበላችኋል። ፖሊሲ ባንክ ደግፏችሁ ሥራ ሠርታችሁ ካፒታል ስታገኙ፣ አቅም ስትፈጥሩ ማስያዣ ሲኖራችሁ ገበያው ይፈልጋችኋል።

■ ጥያቄ፦ ሥልጠናው የተለዩ ሙያዎች ላይ የሚያተኩር (በእስፔሻላይዜሽን ያለው) ላይ ቢሆን አያዋጣም?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ አሁን እያሠለጠን ያለነው ባለቤት የመሆን እምቅ አቅም ያላቸውን ሥራ ፈጣዎች ነው። እናንተ ወደ ሥራ በስፋት ስትገቡ ልዩ ሙያ(ክህሎት) ሥልጠና የሚፈልጉ ተቀጣሪዎች ይኖራሉ። ወደፊት ደግሞ ሠራተኞችን የምናሠለጥንበት ሁኔታ ይኖራል። የቴክኒክ ሥልጠና እንሠጣለን። የሂሳብ፣ የሰው ኃይል፣ የቢዝነስ አስተዳደር፣ የገበያ ወዘተ ባለሙያዎች በተለየ መልክ የምናሠለጥን ይሆናል። በሙያው የተመረቁ ቢሆኑ እንኳን ለእንደዚህ ዓይነት ድርጅቶች አሠራር በሚስማማ መልኩ እንዴት የፋይናንስ ወይም የሰው ኃይል ወይም ሌላ አስፈላጊ የሆኑ ሥልጠናዎችን እናዘጋጃለን። ድርጅቱም ከተቋቋመ በኋላም የምንጓዘው አብረን ነው። ስለዚህ ሥልጠናው ይኖረናል በሚለው ይያዝ።

■ ጥያቄ፦ ባንኩ ለገጠሩ ኅብረተሰብ ብድር ለማቅረብ ያለው ዝግጁነት ምን ያህል ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ የገጠሩን ኅብረተሰብ የእርሻውን ችግር ሳንፈታ ሀገርን ዘመናዊ ማድረግ አይቻለም። እርሻው ያለው በትናንሽ መሬቶች ላይ ታስሮ ነው። ምርታማነቱ በጣም ዝቅተኛ ነው። የሰው ጉልበት አላግባብ እየባከነ ነው። ገበሬው በጠዋት ተነሥቶ የሚደክምባት በዚያች ትንሽ መሬት ላይ ነው። ዘመናዊ መሣሪያ አይጠቀምም። ያለው ሁኔታ አቅም እንዲፈጥር አያስችለውም። በዚያች መሬት ሠርቶ ጥሩ ሀብት ማግኘት አይችልም። ስለዚህ የተቆላለፈ ነው። እርሱ ሀብት የለውም፤ መሬቱ ሀብት አይሰጠውም። አሁን መንግሥት ችግሩን ለመቅረፍ የኩታ ገጠም የእርሻ ፕሮግራም ጀምሯል። ይሄ እየሰፋ ከሄደ የግብርና ሜካናይዜሽን ሊዝ አጋዥ ይሆናል። ለዚህም ባንኩ የራሱ ፕሮግራም አለው፤ ከኬኤፍ ደብሊው ጋርም የሚሠራበት ፕሮግራም አለው። የእርሻ ማሽነሪዎችን ገዝቶ ያቀርባል። የዚህ ጠቀሜታ በግብርና ሜካናይዜሽን እርሻው የሚካሄድ ከሆነ በኩታ ገጠም ትናንሽ መሬቶችን አንድ ላይ አድርጎ ብዙ ገበሬዎች ብዙ ጊዜ ወስዶባቸው የሚሠሩትን በእርሻ ትራክተሮች በአጭር ጊዜ መታረስ መቻሉ ነው። ሲደርስ ደግሞ በኮምባይን ሃርቨስተር በአጭር ጊዜ የብዙዎችን እርሻ ብክነት ሳይኖር መሰብሰብ መቻሉ ነው። ቀንም ሌትም ለሚደክሙ አርሶ አደሮች ውጤታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ጊዜ ይተርፋቸዋል። በሚተርፋቸው ጊዜ በዶሮ እርባታ ከብት ወይም ንብ እርባታ ለማካሄድ ጊዜ ያገኛሉ። ልጆችም ‹‹አባቴን እርሻ ላግዝ›› ብለው ከትምህርት አይቀሩም። በቀላሉ ትምህርት ቤት ሄደው መማር ይችላሉ።

■ ጥያቄ፦ ከአምስት መቶ ሺሕ ብር በታች ካፒታል ያላቸውን የምትቀበሉት እንዴት ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ከአምስት መቶ ሺህ ብር በታች ካፒታል ያላቸው አነስተኛና መካከለኛ የሚባለውን ደረጃ አያሟሉም። እነሱ የሚታቀፉት ጥቃቅን በሚባለው ነው። ለእነሱ ማይክሮ ፋይናንሶቹ ብድር ያቀርባሉ። እኛ ከማይክሮ ፋይናንስ ደረጃ ብቃታቸውን አሳድገው ለሚመጡ አነስተኛ ለሚባሉት ብድር እናቀርባለን።

■ ጥያቄ፦ የብድሩ ጣሪያ ለሁሉም ፕሮጀክቶች አንድ ዓይነት ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ 35 ሚሊዮን የብድር ጣሪያ አሁን ባለው የውጪ ምንዛሬ ደረጃ ዝቅተኛ ሆኗል። በዚህ ጉዳይ ከፌደራል ባለሥልጣናት ጋር እየተሠራ ነው። ሊጨምር እንደሚችል አስባለሁ። ምን አልባትም በእጥፍ ሊጨምር ይችላል። እናንተ እስከምትመጡ ድረስ ችግሩ ተፍትቶ ታገኙታላችሁ።

■ ጥያቄ፡- የሊዝ ማሽን ግዢ ላይ ይስተዋል የነበረውን የተንዛዛ የግዥ ሂደት ለመቅረፍ በተጀመረው ሪፎርም የተገኘ ውጤት እንዴት ይገለጻል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፡- ባንኩ ሪፎርሙን ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ አሠራሩን አሻሽሎ የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ለሁሉም ደንበኞች ፍትሃዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ተደራሽ እየተደረገ ይገኛል። በተለይም ከማሽን ግዢ ጋር ተያይዞ ይስተዋል የነበረውን የተንዛዛ የግዥ ሥርዓት በማሻሻል የተሻለ የግዢ ሥርዓት እንዲኖር ተደርጓል።

■ ጥያቄ፡- ቀደም ሲል በነበረው አሠራር በሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ወለድ የሚታሰበው ማሽኑ ከተገዛ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ በባንኩ የሊዝ ፖሊሲ ላይ እንዳለ ይታወቃል። ከዚህ



አንጻር ማሽን ተተክሎ ወደ ምርት ባልገባበት ሁኔታ ወለድ እንዲታሰብ ማድረግ አግባብነት አለው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ በተሻሻለው የሊዝ ፖሊሲ ወለድ መታሰብ የሚጀምረው ማሽን ተገዝቶ፣ ወደሚተከልበት ስፍራ ደርሶ መሥራቱ ተረጋግጦና ምርት ማምረት (Commission ከተደረገ ጊዜ ጀምሮ) ሲጀምር ወለድ መታሰብ የሚጀምር በመሆኑ ቀደም ሲል ደንበኛው ላይ የነበረው ጫና በዚህ አሠራር እንዲቀረፍ ተደርጓል። ይህ በመሆኑም ከዚያ በመለስ ያለው ወጪ የባንኩ እንጂ የደንበኛው አይሆንም ማለት ነው።

> “በሊዝ ፋይናንስ የወሰድነው ማሽን ላይ ችግር ቢፈጠር ብድሩ የሚታደስበት ሁኔታ አለ?”

■ ጥያቄ፦ በሊዝ ፋይናንስ የወሰድነው ማሽን ላይ ችግር ቢፈጠር ብድሩ የሚታደስበት ሁኔታ አለ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ለዚህ ብዙ መፍትሔዎች አሉት። አንደኛ ዋስትና የራሱ አለው፤ ሁለተኛው መድን (ኢንሹራንስ) ነው። ከዚያ ሲያልፍ ተንቀሳቃሽ ጋራዦች አሉ። በእነሱ የሚታይበት ሁኔታ ይኖራል። ከዚያ ባሻገር ሲሆን፣ ደግሞ እስከ መተካት (replacement) ሊደረስ ይችላል። ለዚህ ግን የችግሩ ዓይነትና ደረጃ ታይቶ መፍትሔ የሚሰጠው ነው።

■ ጥያቄ፦ ከውኃና መብራት የሥራ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ከክልሎች ጋር ምን ተሠርቷል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባለፉት ሁለት ዓመታት ትኩረት ሰጥተን ከሠራናቸው ሥራዎች አንዱ የመንግሥት አካላት ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ያላቸው ትኩረት እንዲጨምር ቢሮክራሲው እንዲቀንስ አስፈላጊው ነገር እንዲደረግ እየሠራን ነው። በሥልጠና መክፈቻው ንግግር ያደረጉ የክልል ሥራ ኃላፊዎች የገቡትን ቃል ማስተዋል ችላችኋል። እኛም በየክልሎቹ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላት ጋር በመሆን በመነጋገር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር እየሠራን ነው። በየክልሉ ዐቢይ (ስቲሪንግ) ኮሚቴ ተቋቁሟል። ልማት ባንክ የኮሚቴው አባል ነው። ኢንተርፕራይዝም አባል ነው። ንግድና ኢንዱስትሪም አባል ነው። የየክልሎችም ምክትል ፕሬዝዳንቶች የሚመሩት ነው። እዚያ ያሉ የኢንቨስትመንት የግብርና የኢንዱስትሪ ቢሮዎች ሁሉ አባላት ናቸው፤ ግምገማ ይካሄዳል። ብዙ የፖሊሲ ችግሮች እየተፈቱ ያሉት በዚያ ነው። ጠንካራ ቅንጅት አለ። በተለይ የኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ደግሞ በየክልሉ የውይይት መድረኮች እያዘጋጀ ይገመግማል። ልማት ባንክ በዚያ ግምገማ ስለሚገኝ ችግሮች ይቀረፋሉ። የተገኙ መፍትሔዎች በዚያ መድረክ በሚደረግ ግምገማ የተገኙ ናቸው። በአመዛኙ ውጤት የተገኘበት ነው። ሂደት ላይ ስለሆንን አንዳንድ ቦታዎች ችግሮች ቢኖሩ በቀጥታ የሚቀረፉ ናቸው።

■ ጥያቄ፦ በሊዝ ፋይናንስ ከልማት ባንክ ተጠቃሚ ሆነን ሳለ ለሥራ ማስኬጃ ከሌሎች ባንኮች ብድር መጠየቅ እንችላለን?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ከሃያ በመቶ በላይ የመሥሪያ ካፒታል መሸፈን የሚችል ኢንተርፕራይዝ ከሆነ ነገር ግን ከዚያ በላይም ካፒታል ያላቸው ከሆነ ከፈለጉ የእኛን ማሽን ማስያዣ ሳያደርጉ ከሌላ ባንክ በራሳቸው ማስያዣ ብድር ሊጠይቁ ይችላሉ።

■ ጥያቄ፦ በየክልሉ ላሉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጠና ብታዘጋጁላቸው ሥራውን ሊያግዝ አይችልም?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ በክልል ካሉ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጋር በየጊዜው በዐቢይ ኮሚቴ የምናደርገው ውይይት ችግሮችን ለመቅረፍ በሚያስችል መንገድ በግልጽ የሚደረግ ግምገማ ስለሆነ የሥልጠና ያህል የሚታይ ግምገማ ነው። አስፈላጊ ከሆነ ግን ጥቆማችሁን ወስደናል፤ የእነሱን ፍላጎት አይተን ሥልጠናዎች ሊኖሩን ይችላሉ።

■ ጥያቄ፦ የባንኩ ወለድ ሊሻሻል ይችላል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንካችን የፖሊሲ ባንክ በመሆኑ የሚሻሻልበት አጋጣሚ ብዙ ላይታይ ይችላል። ነገር ግን ስትራቴጂክ ዘርፍ ብለን የለየናቸው አሉ። ለምሳሌ ዘይት ላይ፤ የዘይት ግብዓት ለሚያመርቱ አሁን ከሚታሰበው ወለድ ለመቀነስ ዕቅድ ይዘናል። ሌላው ስንዴ ነው። ለፓስታው ለመኮረኒው ግብዓት ነው። ከዚህ ጋር ለተያያዘው ለመቀነስ ዕቅድ ይዘናል። ይህን መሰል ስትራቴጂክ ሚና ላላቸው ሴክተሮች በተለይ የውጪ ምርትን ለሚተኩ ዘርፎች የምንቀንስበት ሁኔታ ይኖራል።

■ ጥያቄ፦ የእፎይታ ጊዜን በተመለከተ ምን አዲስ ነገር አለ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ከዚህ በፊት በሊዝ ፋይናንስ ኪራይ የሚከፈልበት ጊዜ በየወሩ ነበር። ነገር ግን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ በሚሰበስባቸው የውይይት መድረኮቻችን ካየነው በኋላ በየሩብ ዓመቱ እንደ ሁኔታው እየታየ በየስድስት ወሩም የሚሆንበት አሠራር ተዘርግቷል። ስለዚህ በስድስት ወር ኪራይ የሚከፈል ከሆነ የእፎይታ ጊዜ እስከ ስድስት ወራት ይኖራል።

■ ጥያቄ፦ ቢሮክራሲው ፈጣን ምላሽ ለመስጠት ምን ያህል ዝግጁ ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ አንዱ ከፍተኛ ማሻሻያ ካደረግንባቸው ጉዳዮች አንዱ የተበላሸን ቢሮክራሲ ማጥፋት ነው። ባንኩ ትልቁ ጠላቱ አድርጎ እየሠራበት ያለው ጉዳይ ሌብነትን መግታት ነው። በዘመድ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት መሥራትን ማጥፋት ነው። አንድ ሰው ራሱ ካልገባበት በስተቀር በሥራው የማግኘት ሙሉ መብት አለው። ባለፉት በ 2ኛ ዙር ሠልጥነው የቀረቡ ፕሮፖዛሎች ታይተው ምላሽ የሰጠነው በሁለት ወራት ውስጥ ነው። በሁለት ወራት እየጨረስን ያለነው ከዚህ በፊት ሁለት፣ ሦስት ዓመታት የሚወስዱ ነገሮችን ነው። ይህንን ስናደርግ ማንም ቢሆን ሥራው እንጂ ማንነቱ በማይታወቅበት ምዘና ነው። ማንኛውም የሚሠራ ነገር ከፕሬዝዳንቱ፣ ከምክትል ፕሬዝዳንቱ እይታ ውጪ ሊሆን አይችልም። በራሳችሁ እናንተ ካልገባችሁበት በስተቀር በዚህ በኩል ያለውን ችግር እያጠፋን ነው። እናንተም በዚህ የጥፋት መንገድ መምጣታችሁ (መቅረባችሁ) ከታወቀ ፕሮጀክታችሁ ይሠረዛል። እንዳትታለሉ፤ መብታችሁን አሳልፋችሁ አትስጡ። ሀገራችሁንም አታበላሹ። ቀጣዮቹን ዙሮችም በተሻለ ሁኔታ እንሠራለን። ስለዚህ በተቻለ መጠን ፕሮፖዛላችሁን ካቀረባችሁ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤቱን ትሰማላችሁ።



■ ጥያቄ፦ በእርባታ ዘርፍ ለመሰማራት ለሚፈልጉ በገጠር መሬት ማግኘት ይችላሉ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ የእንስሳት እርባታ እኛ ለመፍታት ከምናተኩርባቸው ችግሮች አንዱ ነው። የከብት፣ የበግ፣ የዶሮ እርባታ ሲባል እኛ ባለመሥራታችን ደሀ የሆንባቸው ዘርፎች ናቸው። ገጠር መሬት ካላቸው ደግሞ የበለጠ ምቹና ሰፊ የመሆን ዕድል አለው። ዋናው ፕሮጀክት ሆኖ ይምጣ። እንደገፋለን፤ ዋናው በገጠር ያለው ቦታ ለዚያ የተዘጋጀ መሆኑን ማረጋገጥ ነው፤ እርባታ እንደውም ከከተማ ይልቅ ገጠር ቢሆን የሚበረታታ ነው።

■ ጥያቄ፦ ባንኩ ከብድር ባሻገር ተጨማሪ የሚሰጣቸው ድጋፎች ምንድናቸው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ አሁን እኛ እንደዱሮው ብድር ሰጥተን ብድር መልሰሃል አልመለስክም ንግግር ብቻ አይደለም የምንሠራው አብረን ነው። አሁን ዲስትሪክቶቻችንንና ቅርንጫፎቻችን ቁጥራቸው ይጨምራል። ዲስትሪክቶቻችን 24 ይደርሳሉ። ቅንጫፎቻችን 108 ይደርሳሉ። እነዚህ ሁሉ በሰው ኃይል ይጠናከራሉ። እነዚህ ሁሉ በዘርፍ ይከፋፈላሉ። ዘርፎችንም በእስፔሻላይዜሽን ተከፋፍለው እንዲመሩ እየተደረገ ነው። የየክልሉን ሁኔታም የሚያጠና በምክትል ፕሬዝዳንት የሚመራ የሪሰርች ክፍል ተቋቁሟል። ሥልጠናዎች ይቀጥላሉ::፡ የክትትል ሥራው አለ። አድጋችሁ ውጤታማ እስከትሆኑ አብረናችሁ ነን። የልማት ባንክ ዓላማ ልማት ነው።

■ ጥያቄ፦ ባንኩ ለአዳዲስ ክልሎችና ለአርብቶ አደሮች ያዘጋጀው የፖሊሲ ማዕቀፍ ካለ ቢብራራ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ መጀመሪያ የባንኩን ባህርይ መረዳት ያስፈልጋል። ራሱ ባንኩ በልዩ ሁኔታ የፖሊሲ ባንክ ሆኖ የተመረጡ ሴክተሮችን ለመደገፍ የተቋቋመ በመሆኑ ሌላ የተለየ ፖሊሲ የሚያስፈልገው አይደለም። በልዩ ሁኔታ ለመደገፍ የሚሠራ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። ራሱ ባንኩ የተለየ ነው። በዚህ ያለው በሌላ ባንክ የማታገኙት ፖሊሲ ነው። ምንአልባት የተለየ ሁኔታ ቢኖር እንኳን ስትራቴጂክ ዘርፎች ባልናቸው ስንዴን፣ ገብስን፣ የዘይት ግብዓትን በመሳሰሉ ዘርፎች ላይ የምንከተለው ማበረታቻ ፖሊሲ ነው።

■ ጥያቄ፦ 20 በመቶውን መሬት፣ የመኪና ሊብሬ ወይም ቤት የመሳሰለው ቢሸፍንስ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ብድሩን የምትበደሩት ከማን ነው? ከባንኩ ከሆነ የምትበደሩት ብድሩ መቶ በመቶ ይሆናል ማለት ነው። እኛው ራሳችን የምናበድር ከሆነ ማድረግ ያለብን መጀመሪያውኑ መቶ በመቶ ለማበደር መዘጋጀት ነው። እንዲህ ከሆነ አድልዎም ይሆናል፤ ሊብሬ ወይም ቤት ያለው የሚበደር ከሆነ ሌላው ተጠቃሚ አይሆንም ማለት ነው። ሊብሬና ቤት ያለው ከሌላ ቦታ ተበድሮ ሊያመጣ ይችላል። እነዚህንም ሰዎች ቢሆን እንዲህ እንዲደርጉ አልመከርም። ካፒታል የለውም ማለት እኮ ዜሮ ላይ ነው ማለት ነው። ስለዚህ 20 በመቶውን ከሌላ ተበድሮ የሚያመጣ ከሆነ ባለዕዳ ይሆናል፤ እዳውን ለእኛም ለሌላ አበዳሪውም ይከፍላል ማለት ነው። ከሳሪ ነው የሚሆነው። እኛ የምንፈልገው መነሻ የራሱ እንዲሆን ነው። 20 በመቶው ይገዳናል ካላችሁ ደግሞ አማራጭ ሰጠናችሁ፤ ዐሥር ሺህም ይዛችሁ ግቡ፤ ተደራጅቶ መሥራት ይቻላል። በጋራ መሥራት ይጠቅማል፤ መተጋገዝ ይቻላል፤ ብዙ ሐሳብ ይገኛል፤ ሳይንሳዊ አመራር ይኖራል፤ ስርቆት አይኖርም፤ ቁጥጥሩ ይጠብቃል፤ ሰውም በየአቅሙ ሊገባበት ይችላል፤ በትንሹ ቢጀመርም ማሳደግ ይችላል፤ መቀጠርም ይችላል፤ ከዚህ ውጪ ከሆነ ርዳታ ነው፤ እኛ ደግሞ ባንክ ነን።

“ ባንኩ ከብድር ባሻገር ተጨማሪ የሚሰጣቸው ድጋፎች ምንድናቸው? ”

■ ጥያቄ፦- የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ባንኩ ጀነሬተር ገዝቶ ለደንበኞች ቢያቀርብ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ከኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ ባንኩ አማራጭ ይዞ እየሠራ ይገኛል። ከዚህ አንጻር የሚቋቋመው ፕሮጀክት አዋጭ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ባንኩ ጀነሬተር በመግዛት የኃይል አቅርቦትን ችግር ለመቅረፍ የሚሠራ ይሆናል።

■ ጥያቄ፦- ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት በበርካታ ባንኮች እየተሰጠ ይገኛል። በባንኩ በኩልስ ምን እየታሰበ ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ በኃይማኖቱ ምክንያት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የባንኩን አገልግሎት ሳይጠቀም እንዳይቀር በባንኩ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። ከዚህ አንጻር በሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ modality ተዘጋጅቷል። በፕሮጀክት ፋይናንሲንግም በተመሳሳይ ከባንኩ የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል አሠራር እየተዘረጋ ይገኛል።

■ ጥያቄ፦ ታዳጊ ክልሎች ትኩረት እንፈልጋለን፤ ጅግጂጋ

በዲስትሪክት ደረጃ እንዲቋቋም ባንኩ ቢወስን፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን ያለነው አንዱ ጉዳይ ፍትሐዊ የሀብት ሥርጭት እንዲኖር ለማድረግ ነው። ክልሎች እንደየባህላቸው፣ እንደየአቅማቸው ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው። ሥልጠናዎችም ስንሰጥ በእነዚህ ክልሎች በራሳቸው ከተማ እንዲደረግ የወሰነው ለዚህም ነው። ከዚህ ቀደም በነበሩ ሥልጠናዎች ከታዳጊ ክልሎች የሚመጡ ሠልጣኞች በጣም ጥቂት ነበሩ። አሁን ግን በየከተሞቻቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ሠልጣኞች እየተሳተፉ ነው።

በእነዚህ ክልሎች ቅርንጫፎች በማስፋፋትም አገልግሎቱን ተደራሽ እያደረግን ነው። ጅግጅጋ በፊት በድሬዳዋ ዲስትሪክት ሥር ነበር። አሁን ግን ጂግጂጋ ራሱን ችሎ ዲስትሪክት እንዲሆን ወስነናል። እንዲሁ ቅርንጫፎች ይኖሩታል።

አስቀድሜ ለሌሎች ጠያቂዎች እንደገለጽኩት ከዚህ በፊት ከሸሪአ ሕግ ጋር የተስማማ (Shariah-compliant) የሆነ አንድ አገልግሎት እንዲኖር እየሠራን ስለሆነ በዚህም ብዙዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በር ከፍተናል።

ድጋፎቻች የሚባሉት ማሠልጠን፣ ገንዘቡን ማመቻቸት፣ ወደ እነርሱ መቅረብ፣ የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ናቸው። ሌሎቹ ግን እንደሌሎቹ የሚደረጉ ናቸው። ለሶማሌ ክልል አመራር ለባንኩ ሥራ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። በጣም ነው የምናመሰግነው። ወደፊትም ተደጋግፈን ያሉ ችግሮችን እንቀርፋለን።

■ ጥያቄ፦ በአይቲ ዘርፍ ሶፍትዌር እና ሰርቨር ለመገንባት የሚቀርቡ ፕሮፖዛሎች በባንኩ በኩል እንዴት ይስተናገዳሉ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ቀድሞ የተፈጠረን ነገር ከማምረት ጋር የተያያዘ ከሆነ በተለመደው አካሄድ በፕሮጀክት መልክ ፋይናንስ ይደረጋል። 20 በመቶውን አዋጥቶ ማለት ነው። እንደማንኛውም ፕሮጀክት የሚታይ ነው። አዲስ ፈጠራ ሆኖ በሥራ ፈጠራ ሐሳብነት ከመጣ፣ የፈጠራ ባለቤትነት ማረጋገጫ ያለው ከሆነ ባለው አሠራር ውስጥ አልፎ መቶ በመቶ ፋይናንስ እናደርጋለን ማለት ነው።

■ ጥያቄ፦ ከሌሎች ባንኮች ለትምህርት የሚሰጥ ብድር ሥራ ማስኬጃ ብቻ ነው። ከዚህ አንጻር የትምህርት መስክን በሚመለከት አዳዲስ የትምህርት ማእከላትን እንደፕሮጀክት ለመገንባት የሚያስችል ፕሮፖዛል ቢቀርብ በባንኩ በኩል እንዴት ይስተናገዳል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ እኔ ትምህርት ፋይናንስ ይደረግ ሲባል የሚገባኝ ወደ ገጠሩ ሄደን ወደ ትናንሽ ከተሞችም ገብተን እንድንሠራ እየጠየቃችሁ እንደሆነ አስባለሁ። ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው። ትምህርትን ግን በቢዝነስ መልክ ፋይናንስ ማድረግ ሲታሰብ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ በላይ ያለውን ገበያው ራሱ ፋይናንስ ያደርገዋል። ችግር ያለው ከዚያ በታች ባሉት ነው፤ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ያለውን ግን የመንግሥትን በጀት የሚፈልግ ነው። ከተለያዩ እርዳታ ድርጅቶችም ጋር ሆኖ የሚሠራቸው ሥራዎች ናቸው። እኛ የምናበድር ከሆነ አትራፊ መሆን አለበት፤ ከዚያ ብድሩን መመለስ አለበት። ይህ ደግሞ አዋጪ የሚሆንበት ዕድል ብዙም ስላልሆነ እዚህ ውስጥ አንገባም። የሌላው የመንግሥት አካል ሥራ ነው።

የግሎቹ የመጀመሪያ ደረጃና ቅድመ መደበኛ ትምህርትም ላይ ገብተው የሚሠሩበት ሁኔታ እንዳለ እናውቃለን። እርሱን ገበያውም የሚያስተናግደው ስለሆነ ብዙም የምንገባበት አይደለም። እንግዲህ ወደፊት አሁን ትኩረት በሰጠናቸው ዘርፎች ካፒታል እየተፈጠረ ሲመጣ የትኩረት አቅጣጫ መቀየር ሲያስፈልገን ወደዚያ ልንገባ እንችል ይሆናል። ልማት ባንኮች የሚያተኩሩት ወሳኝ ብሎ መንግሥት በለያቸው ላይ ይሆናል። በሂደት ግን ኢንዱስትሪው ከነበረ ትኩረታቸው ኢንዱስትሪ ራሱን እየቻለ ሲወጣ፣ ግብርናውም ራሱን እየቻለ ሲወጣና የልማት ባንክን ልዩ ድጋፍ የማይፈልግበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ይችላል። ገበያው ራሱ ያስተናግደዋል። ሀገራት እያደጉ ሲሄዱ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ዘርፎች እየተለወጡ ይሄዳሉ። ስለዚህ ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም ሌላ ባለቤት እንዳለው ይታወቅ። የተሻለ ሊሠራ የሚችል ባለቤት አለው።

■ ጥያቄ፦ ከዓመታት በፊት በባንኩ ታይቶ የነበረው ኢ-ፍትሐዊነት የሚታይበት አገልግሎት አሰጣጥን ለመቅረፍ ባንኩ እያደረገ ስላለው ጥረት ቢብራራ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ከፍትሐዊነት ጋር ተያይዞ ለውጥ ለማምጣት ባለፉት ሁለት ዓመታት በባንካችን እየተደረገ ያለውን እንቅስቃሴ ክልሎች በቅርበት ያውቁታል። የትኛውንም የሚቀርብልንን የልማት ጥያቄ የምናስተናግደው በፕሮጀክቱ አዋጪነት (ሜሪት) ነው። በተለያዩ ምክንያቶች ተደራሽ ላልሆኑ ሁሉ መረጃዎች እየሠጠን፣ ሥልጠና እየሰጠን፣ ሥልጠና ማእከላቱንም ወደ እነርሱ እያቀረብን፣ ከክልል ባለስልጣናት ጋር የተለየ ውይይትም እያደረግንና ኢንቨስተሮችን እንዲመጡ ወጣቶቻቸውን እንዲያነቃቁ እያደረግን ፍትሐዊነት እየፈጠርን ነው። ቤኒሻንጉልም በዚሁ መንገድ ተደራሽ እየሆነ ያለ ክልል ነው። አሁን በአሶሳ በርካታ ሠልጣኞች እየተሳተፉ ነው። ክልሉ ደግሞ የመሥሪያ ቦታ እና በመሳሰሉት በመደገፍ የበለጠ ሥራ ውስጥ እንዲገቡ ካደረገ የበለጠ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል። የባንኩ ብቻ ሳይሆን የክልሉም ሥራ ነው።

■ ጥያቄ፦ በቤኒሻንጉል ወርቅን ጨምሮ በርካታ ማእድናት ሀብት አለ፤ በዚህ ላይ የተሰማሩ ብዙዎች ባለሀብቶች አሉ። ልማት ባንክ በዚህ ረገድ ያለው ትኩረት እንዴት ይገለጻል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ቤኒሻንጉል ወርቅ በስፋት ሊገኝበት የሚችል አካባቢ ነው። ስለዚህ ወጣቶች ተደራጅተው ከመጡ ለሥራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን እናቀርባለን። ሌሎችም ማዕድናት ላይ እንዲሁ። በተጨማሪም የቤኒሻንጉል ክልል ከሕዳሴው ግድብ ጋር ተያይዞ የዓሣ ማምረት ዕድልም

አለው። የቀርክሃ ደን ማስፋፋትም የሚቻልበት ነው። ባንኩ ከዚህ የሚበልጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች የሉትም። ፍትሐዊነት ለማስፈን ግን በየበኩላችን ድርሻችንን በአግባቡ መወጣት ያስፈልጋል። አዋጪ ፕሮጀክቶችን ማቅረብ ያስፈልጋል። ለዚህም በጋራ እንሠራለን።

■ ጥያቄ፡- የከበሩ ማዕድናት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ለባንኩ ጥያቄ የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞችን ባንኩ በልዩ ሁኔታ ድጋፍ ቢያደርግስ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ የከበሩ ማዕድናት ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ለባንኩ ጥያቄ የሚያቀርቡ ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ የእሴት መጨመር (Value addition) ጉዳይ እስከተጠበቀና ኢንተርፕራይዞቹ የሚጠበቅባቸውን የድርሻ መዋጮ ማዋጣት እስከቻሉ ድረስ ባንኩ ብድር ወይም የካፒታል እቃ ኪራይ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ነው። ነገር ግን ዘርፉ አዋጭ ስለመሆኑ የተረጋገጠ መሆን አለበት። ከዚህ አንፃር የባንኩ ዓላማ ውስን የሆነውን የሀገር ሀብት የጎላ ሀገራዊ ጠቀሜታ ላላቸው ዘርፎች ማበደር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚሰጠው ብድር ተመላሽ ሆኖ ለሌሎች ታዳጊ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጥ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል። ለዚህም ሁሉም ኢንተርፕራይዞች ውጤታማ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

■ ጥያቄ፦ የገጠር መሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርድ መያዣ ተደርጎ ብድር ለምን አይሰጥም?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ መጀመሪያ እኛ የሰው መሬት ለምን እንይዛለን። ማስያዣ እኮ አልጠየቅንም። እንደ ንግድ ባንክ መጠየቅ አይገባንም። እኛ ልማት ባንክ ነን። እኛ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት አንይዝም። በሊዝ ፋይናንስ ምናችሁንም ሳንይዝ ብድር እንሰጣችሁ እያልን ነው። የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ያለው መሬቱ ላይ ሥራ ይሥራ እያልን ነው። በፕሮጀክት ሲሆን ከመሬት ጋር የተያዘዘው ነገር የሚታይበት ሌላ ሁኔታ አለ። በሊዝ ግን ይህ ዓይነት ጉዳይ የለም።

■ ጥያቄ፦ በጋምቤላ ተወስደው የነበሩ ብድሮችን ለማስመለስ ምን እየተሠራ ነው፤ ከክልሉ አመራርስ ጋር ምን ያህል ተናቦ እየሠራ ነው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ጋምቤላ ከባንኩ ጋር የተለየ ታሪክ ያለው ባንክ ነው። ብዙ ነገሮችን አስተናግዷል። ችግሩን ለመፍታት በተለየ መንገድ እየተሠራ ነው።

ከ156 በላይ ፕሮጀክቶች አሉ። ጥቂቶቹ ብቻ ሥራ ላይ አሉ። የአንዳንዶቹ ሰዎች የሉም። ብድሩን የወሰዱ ሰዎች ብድሩን እንዲመልሱ ግን እየሠራን ነው። የጠፉትን ደግሞ ፕሮጀክቱን ወስደን ለሌሎች ባለሀብቶች ሰጥተን እንዲጠቀሙ እያደረግን ነው። ከክልሉ አስተዳዳር ጋር መወያየት ያለብን ክልሉ እንዲለማ ከግብርና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን መነጋገር አለብን። ክልሉን ለመጥቀም ሲባል። ባለሀብቶቹ ጥለዋቸው የሄዱትን መቀማትና ወደ ሥራ መመለስ እንችላለን።

ጋምቤላ ከፍተኛ እምቅ ሀብት በተለይ ለእርሻና ማዕድን ልማት የሚሆን ሀብት ያለው ነው። ነገር ግን በተሠራው አግባብ ያልሆነ ሥራ የባንካችንን ስም ሁሉ ያጠፋ ሥራ ተሠርቷል። ይህንን ቆሻሻ ለማጽዳት ከክልሉ አመራር እና ባለሀብት ጋር ጥሩ ውይይት አድርገናል። ወደፊትም እናደርጋለን።

የክልሉ አመራር ኢንቨስትመንትን በመደገፍ በኩል ያላቸው አቋምና ከባለሀብቶች ጋር ያላቸው ግንኙነት በጣም ትልቅ ቁርጠኝነት አለበት። ባለፈውም አግኝተናቸው ቃል ገብተውልናል። በዐቢይ ኮሚቴ እኛም በትኩረት ከክልሉ ጋር እየሠራን ነው። ብዙ ችግሮች እንደሚፈቱ ተስፋ አለን።

■ ጥያቄ፦ ሊዝ ፋይናንስ ላይ ተሸከርካሪ ለምን አይሰጥም?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ሊዝ ፋይናንስ ላይ ተሽከርካሪ ለምን አይሰጥም ላላችሁት፤ እኛ ፋይናንስ የምናደርገው ማሽነሪውን ነው። መኪናን በልዩ ሁኔታ ፋይናንስ የምናደርገው በአስጎብኚ ድርጅትነት (ቱር ኦፕሬተርስ) ለሚሠሩ ነው። ለእነሱ ማሽነሪው መኪናው ስለሆነ ያንን እናቀርባለን። ካፒታላቸው ራሱ መኪናው ስለሆነ ነው።

በሊዝ ፋይናንስ ግን ወደ ሥራ የገቡ ሆነው ከሁለት ሦስት ዓመት በኋላ አድገው ተሻሽለው ሲገኙና ሌሎች ድጋፍ ሲጠየቁ ምን አልባት አሳማኝ ከሆነ መኪናም ልናይ እንችላለን። ነገር ግን የሊዝ ፋይናንሲንግ ልዩ ባህሪውን ልታውቁት ያስፈልጋል። ማሽነሪው ሲመጣ ከታክስ ውጪ ነው የሚመጣው። መንግሥት ድጋፍ የሚሰጠው አንዱ በዚህ ነው። መኪና ከመጣ ግን ታክስ ይደረጋል። ስለዚህ መኪና በተለየ መልክ ስለማይሰጥ መኪና የሚገዛው እንደማንኛውም ነው ማለት ነው። በአስጎብኚ ድርጅትነት ግን ከታክስ ነጻ ሆነው መጠቀም ይችላሉ።

■ ጥያቄ፡- ኮንክሪትና ሲሚንቶ በማቡካት በግንባታ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ተቋራጮች ግብዓት ለማቅረብ ጥሬ ዕቃው ከ75% በላይ ሀገር ውስጥ ስለሚገኝ ባንኩ ለዘርፉ ብድር ቢያቀርብ የቻይና ባለሀብቶች የሚሰሩትን ሥራ በተመጣጣኝ ዋጋ መስራት ስለሚቻል ባንኩ Concrete Batching (ኮንክሪትና ሲሚንቶ አንድ ላይ የሚያቦካ ማሽን) በሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት ለደንበኛው ቢያቀርብ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ Batching plant በተመለከተ ፕሮጀክቱ ውጤታማ ሆኖ ሀገር የሚቀይር እስከሆነ ድረስ ባንኩ በሊዝ ፋይናንስኒግ የማሽን ግዢ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ነው። የውጭ ዜጎች የሚሠሩትን ሥራ ሀገር ውስጥ መስራት ከተቻለ በውጭ ምንዛሪ የሚከፈለውን ክፍያ የሚያስቀር አቅም ስለሚፈጥር (Import substitution) እንደ ተኪ ምርት ተወስዶ ባንኩ ድጋፍ የሚሰጥ ይሆናል። ስራው ሀገራዊ አቅምን ለመገንባትም ጭምር ስለሆነ ባንኩ ድጋፍ የሚሰጥ ይሆናል።

■ ጥያቄ፡- ባንኩ ሁልጊዜ ለደንበኞቹ በሩን ክፍት ማድረግ አለበት። በተለያዩ ምክንያቶች ደንበኛው በባንኩ የአገልግሎት




አሰጣጥ ላይ ቅሬታ ስለሚያቀርብ የደንበኛውን ቅሬታ ለማስተናገድ የሚያስችልና ደንበኛው ብሶቱን የሚናገርበት መድረክ ቢፈጠር፤ ተበዳሪዎች በቢሮክራሲው ላይ ተፅእኖ እና ጥቃቶችን በጋራ ለመከላከል በባንኩ በኩል የተበዳሪዎች ማህበር ለምን አይመሰረትም? በማህበሩ አማካይነትም ከባንኩ ጋር በመተባበር የመሠረተ ልማት ጥያቄዎችን ማለትም የኤሌክትሪክ መስመሮችን፣ የመሬት አቅርቦት ጉዳዮችን እንዲሁም ደንበኞች ከባንኩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር አይረዳም?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንኩ ለደንበኞች የመወያያ መድረኮችን (ፎረሞችን) ያዘጋጃል። ይህም በዘርፍ በዘርፉ የሚደረጉ መድረኮችን ይጨምራል፤ ነገር ግን የደንበኞች ማህበር (የተበዳሪ ማህበር) ማደራጀት የሀገሪቷ የንግድ ሥርዓት ስለማይፈቅድ ባንኩ በዚህ ላይ ድጋፍ አይሰጥም። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አሠራርም የተበዳሪዎች ማህበር ማደራጀትን አይፈቅድም። የተበዳሪ ኃላፊነት የግል ስለሆነ የሚወስደው ኃላፊነትም እንደዚያው በግል ይሆናል ማለት ነው። ከዚህ አንፃር በማህበር መደራጀት በሀገሪቷ የሚፈቀደው ሙያን መሠረት አድርገው ለሚደራጁ ግለሰቦች/ ሙያተኞች ነው።

■ ጥያቄ፡- ሥልጠናው ሠልጣኞች በቂ ዕውቀት እንዲያገኙ ረድቷቸዋል፤ ነገር ግን የባንኩ ሠራተኞች ግንዛቤ ኖሯቸው የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰጡ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ተሠርቷል?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንኩ ከኮርፖሬት ጀምሮ እስከ ቅርንጫፍ ድረስ ያሉትን ሠራተኞቹን በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በተለያዩ ጊዜያት ግንዛቤ እንዲኖራቸው አድርጓል። ደንበኛ እንዴት መስተናገድ እንዳለበት፣ ጥሩ ደንበኛ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ወዘተ... በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ተደርጎ መግባባት ተፈጥሯል።

■ ጥያቄ፡- ባንኩ ሪፎርሙን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ አሠራሩን በደንብ ፈትሿል ወይ? በተለይም የቁጥጥር ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ የባንኩ ሠራተኞች አስፈላጊውን አገልግሎት በተገቢው ጊዜ ለደንበኞች ባለመስጠታቸውና በትናንሽ ችግሮች ደንበኛው ችግር ላይ እንዲወድቅ ምክንያት እየሆኑ ስለሚገኙ ከደንበኞች ለሚነሱ ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ ለመስጠትና ተጠያቂነትን ለማስፈን የተሠሩ ስራዎች አሉ ወይ?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፦ ባንኩ በሪፎርሙ ራሱን ተመልክቷል ወይ ለሚለው ጥያቄ አዲሱ የባንኩ ሥራ አስፈፃሚ ወደ ኃላፊነት እንደመጣ የወሰደው እርምጃ የባንኩን አሠራር በዝርዝር መፈተሽ (ማየት) ነበር፤ ቀጥሎም የተለዩ ችግሮችን መሠረት በማድረግ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ ሪፎርም ፕሮግራም እንዲዘጋጅ አድርጓል። የአምስት ዓመቱ ስትራቴጂክ ሪፎርም ዕቅድ ሲዘጋጅም ችግሮቻችን ምንድን ናቸው የሚለውን ጥያቄ በጥልቀትና በዝርዝር ታይቷል። ጎን ለጎንም እያስኬዳቸው ያላቸው ሥራዎች አሉ። ለአብነትም ባንኩ 'ቢዝነስ ሞዴሉን' እየቀረ ይገኛል። ከዚህ በፊት በነበረው ቢዝነስ ሞዴል ሁሉም ዘርፎች (sectors) በአንድ የሥራ ክፍል የሚስተናገዱበት አሠራር ስንከተል ነበር፤ በአዲሱ ቢዝነስ ሞዴል ግን ለእያንዳንዱ ሥራ ልዩ የሥራ ሙያን መሠረት በማድረግ ደንበኛውን ማስተናገድ የሚያስችል አሠራር ተዘርግቷል። ለምሳሌ ለዶሮ እርባታ



ብድር መስጠት ካስፈለገ (በዘርፉ ልዩ የሥራ ሙያ ያለው) ባለሙያ ይመደብለታል፤ ለግብርና፣ ለጨርቃጨርቅ፣ ለቆዳ ኢንዱስትሪና ለሌሎች ዘርፎችም እንደዚያው፤ በዚህም የደንበኞችን ፍላጎት በቀላሉ መረዳት የሚችሉ ባለሙያዎች ይኖራሉ ማለት ነው።

■ ጥያቄ፡- የካፒታል ዕቃ ኪራይ አገልግሎት ለባንኩ እና ለማኅበረሰቡ አዲስ አገልግሎት እንደመሆኑ መጠን ማሽን ሲበላሽ በባንኩ እና በአቅራቢው መካከል እንዲሁም በአቅራቢውና በማሽን አምራቹ (Manufacturer) መካከል መኖር የሚገባው ግንኙነት በፖሊሲ ላይ በግልጽ ቢቀመጥ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፡- ማሽነሪዎች ሲበላሹ ለጥገና ሥራ ረጅም ጊዜ እንዳይወስድ ተንቀሳቃሽ ጋራዦች (mobile ga-rage) እንዲኖሩ ከክልሎች ጋር እየተመከረበት ይገኛል። በተለይም የእርሻ ማሽነሪዎች በቅርበት ጥገና አገልግሎት እንዲሰጣቸው ተንቀሳቃሽ ጋራዦች በየቦታው እንዲከፈቱ ይደረጋል። ረጅም ጊዜ የሚወስደውን የማሽን ጥገና ሂደት አሠራሩን በማሻሻል አጭርና ቀልጣፋ እንዲሆን ይደረጋል።

■ ጥያቄ፡- የባንኩ አሠራር አሁንም በዋና መ/ቤት ደረጃ የተወሰነ ነው፡ ፤ በተለይም ከማሽን ግዥ፣ ከመሠረተ ልማት ጥያቄዎች፣ የማሽን ጥገናና የመለዋወጫ ዕቃ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ጥያቄው ወደ ዋና መ/ቤት የሚገፋበት ሁኔታ ስላለ ሥራው ወደ ዲስትሪክት እና ቅርንጫፎች እንዲወርድ የአቅም ግንባታ ሥራ ቢሠራ፤

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፡- ዲስትሪክቶች ከ150 ኪ.ሜ በላይ እንዳይራራቁ ለማድረግ በአዲሱ አሰራር (በዲስትሪክት እና ቅርንጫፍ ምጣኔ) ታስቦበት ተሠርቷል። በቅርብ ጊዜ ውስጥም ተግባራዊ ስለሚደረግ ባንኩ አገልግሎቱን በቅርበት ተደራሽ እያደረገ ነው። በዚህም እታች ድረስ ደንበኛው ጋር በመሄድ የኢንቨስትመንት ሥራውን ለመደገፍ ባንኩ ተጨማሪ ዲስትሪክቶች እና ቅርንጫፎችን ለመክፈት ወስኗል።

■ ጥያቄ፡- የሊዝ ፋይናንሲንግ አገልግሎት የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ቅንጅት የሚጠይቅ ሥራ እንደመሆኑ መጠን ከባለድርሻ አካላት ጋር ባንኩ በቅንጅት ለመሥራት እቅድ አለው?

ዶ/ር ዮሐንስ አያሌው፡- ባንኩ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጥሩ ግንኙነት ፈጥሮ እየሠራ ይገኛል። ለአብነትም የመሠረተ ልማት አቅርቦቶችን፣ የመሬት ምዝገባ፣ የመሥሪያ ቦታ አቅርቦት እና ወዘተ ላይ ባንኩ ከክልል እና ከፌዴራል መንግስት የሥራ ኃላፊዎች ጋር ውይይቶችን እያደረገ ይሠራል። በተለይም የሊዚ ፋይናንሲንግ አገልግሎት በአዲስ መልክ ለማስጀመር በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሊዝ ፋይናንሲንግ ዐቢይ ኮሚቴ ኮሚቴ ተዋቅሮ ባንኩ በቅንጅት ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየሠራ ይገኛል።

አመሰግናለሁ!



የኢትዮጵያ ልማት ባንክ
የልማት አጋርዎ !

+251 11 551 1188/9
Josef Tito St., Addis Ababa, Ethiopia
dbe@ethionet.et
www.dbe.com.et